የሰ/መ/ቁ. 23628

ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ብርሃኑ አመነው

ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ ጠበቃ ከበደ ወርቄ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ-ጠበቃ ያሲን እንድሪስ

2ኛ. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነ/ፈጅ በቀለ ተፈራ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበው የአሁኑ አመልካች መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ አመልካች በሰበር ቅሬታ ማመልከቻው፣ለክብሪት ሥራ የሚያገለግለውን የመቀስ የንግድ ምልክት እ.ኤ.አ. ከ1921 ጀምሮ በቼክ ሪፑብሊክ የንግድ ምልክቶች መ/ቤት በማስመዝገብ ባለቤትነቱን አስከብሮ መቆየቱን ገልጾ በኢትዮጵያም ውስጥ ምልክቱ እንዲመዘገብለት የአሁኑን 2ተኛ ተጠሪ ጠይቆ ምዝገባው እንዲፈፀም ወስኖ በሂደት ላይ ያለ መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰው የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ለኔ ይገባል ሲል የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ አቅርቦት የነበረውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ መሆኑን፤ሆኖም አንደኛ ተጠሪ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ ክስ መመስረቱን፤በተከሳሽነት የቀረበው የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ብቻ በመሆኑ በክሱ የሚነሱት ጭብጦች አመልካችን በቀጥታ የሚመለከቱ በመሆናቸው በክርክሩ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር እንዲፈቀድለት ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የንግድ ሕግ ቁጥሮች 100፣107፣219፣222 እና 223 ን በመጥቀስ የአሁኑ አመልካች ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላልተመዘገበ



የሕግ ሰውነት የለውም፡፡ የሕግ ሰውነት ከሌለው ደግሞ ፍ/ቤት ቀርቦ ለመከራከር አይችልም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የበታች ፍ/ቤት ውሳኔን እንዳለ አፅድቆታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት ሚያዚያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት፣የአሁኑ አመልካች በኢትዮትያ ውስጥ አልተመዘገበም በሚል አቅርቦት የነበረው የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሠበር እንዲቀርብ ወስኖ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡

በመሠረቱ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አመልካች እዚህ አገር በነጋዴነት ያልተመዘገበ ስለሆነ ፍ/ቤት ቀርቦ ለመከራከር አይችልም በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ለውሳኔውም መሠረት ያደረገው የንግድ ሕግ ቁጥር 100 እና የሚቀጥሉትን አንቀጾች በመጥቀስ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የንግድ ሕግ ቁጥር 100 እና የሚቀጥሉት አንቀጾች የሚናገሩት ስለምዝገባ ቢሆንም፣የምዝገባ አስፈላጊነት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራን ለማካሄድ በዋነኛነት መከናወን ከሚገባቸው መስፈርቶች አንዱ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የንግድ ሥራ መሥራትና የንግድ ምልክትን ማስመዝገብ የተለያዩ ተግባራት መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡ አመልካች የንግድ ምልክትን በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመዘገብለት ጠይቆ ጉዳዩ በሂደት ያለ ስለመሆኑ የአሁኑ በሰበር 2ኛ ተጠሪ የሆነው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያረጋገጠለት ስለመሆኑ ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የአሁኑ አመልካች በውጪ አገር ሕግ ተመዝግቦ የሕግ ሰውነት ያለው ኩባንያ መሆኑ ከተረጋገጠና በዚህ ባገኘው የሕግ ሰውነት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ ቢያነሳ ቀደም ሲል በሌላ አገር የተጎናፀፈው የሕግ ሰውነት እንደሌለ ይቆጠራል የሚያሰኝ ሊሆን አይገባም፡፡

በዚህ መሠረት የአሁኑ አመልካች በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 41 መሠረት በጉዳዩ ያገባኛል የሚልበትን ምክንያትም የመብቱን ሁኔታ በዝርዝር ገልጾ የነበረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ከጥያቄው ጋር አግባብነት የሌላቸውን የሕግ ቁጥሮች ጠቅሶ የጣልቃ ገብነቱን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

- የፌ.መ.ደ.ፍ/ቤት በመ/ቁ.3312 በሰኔ 07 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ብይን እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.32181 በጥር 26 ቀን 1998 የሰጡዋቸው ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡
- ይህ ችሎት አመልካች በጉዳዩ ጣልቃ ገብ ሆኖ ለመከራከር የሚያስችለው መብት ያለው ወገን መሆኑን በመቀበል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ጉዳዩን መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.343/1/ መሠረት መልሶለታል፡፡
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰበር መ.ቁ. 23692

ሐምሌ 03 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ አቶ ጉሳዬ ጉርሙ ቀረቡ፡፡**

**መልስ ሰጭዎች፡- እነ አሊ መሐመድ - አልቀረቡም፡፡**

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የጉዳዩም መነሻ ነገር የአሁን መልስ ሰጭዎች ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ላየው ለጌዲኦ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት የጉዳት ካሣ ክስ በአራት ተከሳሾች ላይ አቅርበዋል፡፡ 1ኛው ተከሣሽ አበባ ኃ/የተ/የግል ማህበር እራሱን በሚመለከት የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር ካቀረበ በኂላ ጉዳት አድርሷል የተባለው መኪና በሌላ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የአሁን አመልካች አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ካሣ ለመክፈል እስከ ብር 30,000.00 የመድን ሽፋን የሰጠበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት ገብቶ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ይታዘዝልን በማለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሠረት የአሁን አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ደረሰ ለተባለው ጉዳት 1ኛ ተከሳሽ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንና በካሣው መጠንም ረገድ አለኝ የሚለውን የመከራከሪያ ነጥብ በማንሣት ተከራክሯል፡፡